# የ "ሎፋ" ወረፋ እና የዶ/ር መረራ ትንቢቶች

በመሐመድ ሰልማን

ፌዝ ይቀናቸዋል፡፡ ዶ/ር መራራ ኑሮ ለመረረው ህዝብ ስላቅ የበዛበት ፖለቲካ መመገብ ይወዳሉ፡፡ እርሳቸው ድሮም እንዲህ ናቸው፡፡ ፓርላማ ሳሉም፤ ከፓርላማ ውጭም በኢህአደግ እየተሳለቁ ነው የሚታገሉት፡፡ ፌዝ፣ ቧልት፣ አሽሙር፣ ሽሙጥ፣ አግቦ ይዋጣላቸዋል፡፡ ከወራት በፊት ለአንድ ጋዜጣ ..እኔ ቢራ እየጠጣሁ ነው መታገል የምወደው.. ብለውት ነበር፤ እቅጩን፡፡ ሆኖም በስነ ምግብ ህግ መሰረት ቢራ ለመጠጣት ምግብ መቅደም አለበት፡፡ በዚህ ስሌት ዶ/ር መራራ እታገልለታለሁ የሚሉት ህዝብ ለአቅመ ቢራ እንኳ አልደረሰም፡፡

ከሁለት ሳምንታት በፊት ዶ/ር መራራ "አውራምባ ታይምስ" ለተባለ ሳምንታዊ ጋዜጣ እንዲህ አሉት፡-
"ረሀብ አዲስ አበባ ውስጥ አለ፡፡ ከቆሻሻ መጣያ ገንዳ ምግብ አውጥቶ የሚበላ ስንት ሰው ነው? ረሃብ ማለት የምግብ እጦት ማለት ነው፡፡ ሌላ ፍልስፍና አያስፈልገውም እኮ፡፡"
ዶክተሩ እውነታቸውን ይሆን? በመዲናችን ረሀብ አለ? ይህንኑ ለማረጋገጥ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ለቀናት ሸው እልም ማለት ሳይኖርብን አይቀርም፡፡

## ገንዳ - ላይፍ

የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ጽዳት አይሆንላቸውም፡፡ አንድ ጋሽ አበራ ሞላ ከተዋቸው በኋላ ደግሞ ብሰባቸዋል፡፡ በየጥጋ ጥጉ የሚታዩ የቆሻሻ ክምሮች እንደ ዘመኑ የቀበሌ ጽ/ቤት ፎቆች ቦታ ሳይመርጡ ደርሰው ይቆለላሉ፡፡ የቆሻሻ ክምሮች አስታዋሽ ሲያጡ የቆሻሻ ፎቆች ይሆናሉ፡፡ አገሪቱ የቆሻሻ ክምሮችን በየአደባባዩ በማሳየት የቱሪዝም ገቢ የምታገኝ ነው የሚመስለው፡፡ በነዚህ ክምር የቆሻሻ ቁልሎች ውስጥና ውጭ እንደቆሻሻ የተረሱ ዜጐችን አስተውላችሁ ይሆን? 24 ሰዓት አይጠፉም፡፡ ንክ ሆነው አይደለም፡፡ በቆሻሻው ገንዳው ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ እየፈለጉ ነው፡፡ ረሀብ ጊዜ አይሰጥም፡፡ እንደ ዝንጀሮ ከአንድ ገንዳ ወደ ሌላኛው ይስፈነጠራሉ፣ እንደፍልፈል ይፈለፍላሉ፣ እንደ ጎተራ አይጥ ይሽሎኮሎካሉ፡፡
በነዚህ ገንዳዎች አቅራቢያ የሚያልፉ የተሳካላቸው ዜጐች በመጥፎ ጠረኑ ይሞቱ ይመስል አፍንጫቸውን ጠፍንገው በመያዝ ቶሎ ቶሎ እልፍ ይላሉ፡፡ ከገንዳው የሚወጣው መጥፎ ጠረን ለደቂቃም አያስቆምም፡፡ በዚህም ምክንያት በገንዳው ውስጥ ያለውን ህይወት ለማየት የሚታደሉት ጥቂቶች ናቸው፡፡
በቆሻሻ ገንዳዎቹ ውስጥ እየቀዘፉ የሚላስ የሚቀመስን ፍለጋ የሚናውዙ ዜጐችን ቆም ብለው የሚያስተውሉ ብጹአን ዜጎች ግን በሚያዩት ነገር አንቅጥቅጥ (shoke) ላይፈጠርባቸው አይችልም፡፡ በእርግጥም ገንዳው ውስጥ ያሉትን ዜጐች ቀልብ ገዝቶ የሚያስተውል ሰው ስሜቱ የሚረበሸው ከመቅጽበት ነው፡፡ በሚከረፋ ጠረን የተሞላ የቆሻሻ ገንዳ ውስጥ ከቆሻሻ የተሰራ ሰው ማየት ምንኛ ያስጨንቃል፡፡ የሰው ልጅ ክቡር ነው፤ ቢያንስ ከቆሻሻ ከፍ ያለ ፍጥረት ነው፡፡ እንደ ዝንብ ገንዳ ውስጥ ምግብ የሚያድኑ ዜጎቻችን ቁጥር እያሻቀበ መምጣቱ ጥሩ ምልኪ አይመስልም፡፡ ወዴት እያመራን ነው?
አትክልት ተራ በየማለዳው አቅሏን ትስታለች፡፡ በረሃብ አቅላቸውን የሳቱ ዜጐች በአካባቢው በብዛት በሚቀመጡ ገንዳዎች ውስጥ እንደፍልፈል ይሽሎኮለካሉ፡፡ የበሰበሱ ማንጎዎችን፣ በከፊል የተገመጡ አናናሶችን፣ ቁራጭ ሙዞችን፣ ፍፁም የተበላሹ ቲማቲሞችን፣ ትላትል የወረራቸው አቦካዶዎችን ከቆሻሻ ገንዳዎቹ ሲያገኙ ፊታቸው በፈገግታ ይደምቃል፡፡ ከነዚህ ዜጐች ውስጥ ጥቂቶቹ የአእምሮ በሽተኞች ሲሆኑ፤ ጥቂቶቹ ጤኔ እና ችጋር ለአእምሮ በሽታ የዳረጋቸው ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ እነዚህን ዜጐች የዓለም የምግብ ድርጅት አልቆጠራቸውም፣ ማዘጋጃ አያውቃቸውም፣ መንግስት አያስባቸውም፣ ዶ/ር መረራ ግን ይፎክሩባቸዋል ወይም ይፎክሩላቸዋል፡፡ "የሚበላውን ያጣ ህዝብ..." እያሉ...

## የ "ሎፋ" ወረፋ......

"ሎፋ ከሚደፋ ተባብረን እንንፋ" ይሉ ነበር የሰፈሬ ልጆች ፤ ድግስ ቢጤ በሰፈር ውስጥ ካዩ፡፡ "ሎፋ" ዛሬ ድግስ አይጠብቅም፡፡ እለታዊ ሆኗል፡፡ ንግድ ሆኗል፡፡ መተዳደሪያ ሆኗል፣ ነፍስን ማቆያ ሆኗል፡፡ ጠ/ሚኒስትራችን በቀን ሶስት ጊዜ ህዝቤን አበላዋለሁ ያሉት ቃል ቢያንስ "ሎፋ" ባይኖር ብዙ ሰፈሮች ውስጥ ባልተሳካላቸው ነበር፡፡ የጠ/ሚኒስትሩ ቃል ታጠፈ የማንለው ሎፋ በመኖሩ ነው ብለን መናገር እንችላለን፡፡ ብዙዎች ከሚገምቱት በላይ ሎፋ በሺ የሚቆጠሩ ከሰው በታች የሚኖሩ ዜጐችን እየታደገ ያለ "ትልቅ ኢንደስትሪ" እየሆነ ነው፡፡ ይህንን አይቶ ለመመስከር ማንኛውም ዜጋ አካባቢውን መቃኘት ብቻ በቂው ነው፡፡ ለምሳሌ መርካቶ ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣ አዲስ መስክ ቢኖር "የሎፋ ኢንደስትሪ" ነው፡፡

ለመሆኑ ኡፋ ምንድነው?

ኡፋ ትርፍራፊ ምግብ ማለት ነው፡፡ ዜጐች በልተው ያስተረፉት ምግብ፣ ቆረጣጥመው የተፉት አጥንት፣ አኝከው ያልዋጡት ስጋ ..ኡፋ.. ወይም ..ቡሌ.. በመባል ይታወቃል፡፡ ከአነስተኛና መካከለኛ ሆቴሎች ከተመጋቢ የተራረፉ ምግቦች ጓሮ በሚቀመጡ ያደፉ በርሜሎች ወይም ጆንያዎች ውስጥ ይደፋሉ፡፡ በርሜሎቹ ወይም ጆንያዎቹ ሲሞሉ ወደ ቆሻሻ ገንዳ ተወስደው አይደፉም፡፡ የኡፋ ደላሎች /ካቦዎች/ እንዲጠሩ ይደረጋል፡፡ የኡፋ ካቦዎች በበርሜል የተሰበሰበውን ምግብ ለሆቴሉ አሳላፊዎች መጠነኛ ጉቦ በመክፈል አልያም ደግሞ ከሆቴል ባለቤቶች በችሮታ በማግኘት ጠቀም ያለ ትርፍ ያገኙበታል፡፡ በኡፋ የተሞላውን በርሜል በጅምላ እንዲወስዱት ይደርጋል፡፡ 2 ጆንያ፣ 3 ጆንያ...

የኡፋ ደላሎች /ካቦዎች/ በርሜሉን ተሸክመው በጉጉት ወደሚጠብቋቸው ምንዱባን ዘንድ ይበራሉ፡፡ የዚያ ሰሞኑን የዘይት ወረፋ የሚያስንቁ ዘለግ ያሉ ሰልፎች ተሰርተው ይጠብቋቸዋል፡፡ ሰልፎቹ የኡፋ ካቦዎቹንና ጆንያዎቹን ሲያዩ መዘበራረቅ ይጀምራሉ፡፡ ጸብ፣ ግብግብ፣ ትንቅንቅ፣ ስድድብ ይጀመራል፡፡ ነዳያን ሲሰዳደቡ ለነገ አይሉም፡፡ ..አንተ መናጢ.... ይባባላሉ እርስ በእርስ፣ ..አንተ ወራባ ስግብግብ ድሃ.. ይለዋል አንዱ የኔ ቢጤ ሌላውን፡፡ እጅ የሌላቸው ቡጢ ለመሰንዘር ይቃጣቸዋል፤ እግር የሌላቸው በጫማ ጥፊ መማታት ያምራቸዋል፡፡ ኡፋውን ማግኘት የሞት ሽረት ትግል ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም ኡፋ የያዘው በርሜል ካለቀ ጦም ማደር ይከተላል፡፡ ሆዱን እያከከ ማደር ማንም አይፈቅድም፡፡ በዚያ የኡፋ ወረፋ ትንቅንቅ ውስጥ አቅመ ደካማ አዛውንት የኔ ቢጤዎች ክፉኛ ሲንገላቱ ማየት ስሜት ይሰብራል፡፡

ሰዓቱ ሲገፋ የኡፋ በርሜሉ /ጆንያው/ እየጎደለ፣ ሰልፈኞች እየቀነሱ ይሄዳሉ፡፡ ሁሉም ነዳያን፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች ፣ የአእምሮ በሽተኞች የሰልፉ ጫፍ ላይ ሲደርሱ እጆቻቸ ውን ወደ ኪሶቻቸው መስደድ ይጀምራሉ፡፡ ስስ ፌስታል ፍለጋ፡፡ የሚገርመው የአእምሮ በሽተኞች እንኳ ይህን ለማድረግ አይሰንፉም፡፡ ጋዝ ለመግዛት የምትሄድ የቤት ሰራተኛ ጀሪካኗን እንደማትረሳ ሁሉ ኡፋ ለመግዛት የሚሄዱ የዝቅተኛው መደብ ዜጐች ፌስታል መያዝ አይረሱም፡፡

ወረፋቸው ሲደርስ ስሱን ፌስታል አስፋፍተው ይከፍቱታል፡፡ የኡፋ ካቦው በበርሜል ወይም ጆንያ ያመጣውን ..ቡሌ.. ለማከፋፈል ጭልፋ አይጠቀምም፡፡ የተፈጥሮ እጁን ወደ በርሜሉ እየሰደደ መዳፉ የቻለለትን ጭብጦ እያፈሰ በተዘረጋለት ስስ ፌስታል ይሰፍረዋል፡፡ በዚያው በሚሰፍርበት እጁ ላቡን ይጠርገዋል፣ አፍንጫውን ያጸዳዳዋል፡፡ ይህ ለተሰላፊዎቹ ብዙም ግድ የሚሰጣቸው አይመስልም፡፡ ተረኛው ተሰላፊ በልቡ አጥንት፣ ቅልጥም፣ ጉማጅ ስጋ እንዲያጋጥመው በርትቶ ይፀልያል፡፡ እድሉ ያለለትን ይዞ አንድ ብር ወይም ሀምሳ ሳንቲም ከፍሎ አካባቢው ከሚገኝ አንድ ጥግ ፊቱን አዙሮ ይበላል፡፡ የብዙዎች አመጋገብ እርጋታ አይታይበትም፡፡ ተስገብግበው ሲበሉ ከዚህ ቀደም ምግብ የሚባል ነገር ጭራሽ በልተው የሚያውቁ አይመስሉም፡፡ ፌስታሏ ከመቅጽበት ባዶ ትሆናለች፡፡ ፌስታሏን አይጥሏትም፡፡ አርገፍግፈው ያራግፏትና መልሰው ወደኪሳቸው ይዶሏታል፡፡

የዩኒቨርስቲው ..ቡሌ..

የ..ቡሌ../ኡፋ ገበያ የመርካቶ ትዕይንት ብቻ አለመሆኑን መረዳት ያሻል፡፡ በሁሉም የከተማው አቅጣጫዎች የቡሌ ኢንዱስትሪ ይገኛል፡፡ መገናኛ ድልድዩ ስር፣ ሰንጋተራ በፈራረሱት ሱቆች መሀል፣ አራት ኪሎ፣ ተክለሃይማኖት፣ በርበሬ ተራ፣ ሃያ ሁለት፣ ወዘተ በአሳቻ ሰዓትና ስፍራ ይቸበቸባል፡፡

በአንድ ወዳጄ ጥቆማ አራት ኪሎ ከዩኒቨርስቲው የሚወጣ ..ኡፋ.. እንዳለ ተነገረኝ፡፡ በተሰጠኝ ጥቆማ መሰረት ምንሊክ ትምህርት ቤት በር ላይ ጫማዬን እያስጠረኩ የቡሌ ሰዓት እስኪደወል ተጠባበቅኩ፡፡ ጫማዬን እያጸዳልኝ የነበረው የወላይታ ተወላጅ ሊስትሮ ..ለምን ፈልገህ ነው? አሁን ይመጣሉ.... አለኝ፡፡ በዚያው ቅጽበት ቡሌው በአምስት ትልልቅ ኩርቱ ፌስታሎች በሰው ጉልበት ተጭኖ መጣ፡፡ አራት ወጠምሻ የጎዳና ተዳዳሪ የሚመስሉ ጎረምሶች የፌስታሉን ጆሮዎች ጫፍ ጫፍ በመያዝ በምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደጅ ላይ ወደሚገኝ አጸድ ውስጥ ይዘውት ገቡ፡፡ ዓለማያ/ሀረማያ/ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳለሁ በግቢው ለሚገኙ ለማዳ ጅቦች በተመሳሳይ መልኩ ትራፊ ምግብ በፌስታል ተጭኖ ይወሰድላቸው እንደነበር ታወሰኝ፡፡ አሁን ይህ እየሆነ ያለው ለሰው ልጆች ነው፡፡

በኩርቱ ፌስታሎች የታጨቀው ቡሌ ሚኒሊክ ት/ቤት ደጅ ላይ ባለች ትንሽ መናፈሻ ውስጥ ሲደርስ ተራገፈ፡፡ ሰማያዊ ክብ ቅርጽ ያለው የህዝብ ስልክ ማስደወያ ብረት ስር ፌስታሎቹ ተቀመጡ፡፡ በአካባቢው ከበው የሚጠብቋቸው ነዳያንና ሌሎች የአነስተኛ መደብ ዜጐች ቢጫ ኩርቱ ፌስታሎቹን ሲያዩ መረባበሽ ያዙ፡፡ መተረማመስ፣ መጎሻሸም፡፡

በቅርብ ሆኜ እንደታዘብኩት አንድ ፌስታል ቡሌ 2 ብር ይሸጣል፡፡ ተመጋቢዎቹ የተሻለ ምግብ እንዲሰፈርላቸው አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ ለጠብ ይገባበዛሉ፡፡ ቡሌው ምን እንደሚመስል ለማየት በአቅራቢያው ጫማዬን ባጸዳልኝ ወላይታው ሊትሮ አማካኝነት አስገዝቼ ቀማምሼዋለሁ፡፡ ማርማራት

የተቀቡ ቁራጭ ዳቦዎች፣ የተጋጡ አጥንቶች፣ የታኘኩ ስጋዎች፣ አንዳንድ ጊዜም ብጣሽ ሶፍቶች በምግቡ ተቀላቅለው ይገኛሉ፡፡
ይህ ወላይታ ሊስትሮ ዘርዝሮ እንዳጫወተኝ ከሆነ የአራት ኪሎው ኡፋ የሚወጣው ከዩኒቨርስቲው ካፌ ሲሆን ቁርስ፣ ምሳ እና እራት ሰዓት ላይ ትራፊው ምግብ በፈስታል እየወጣ ይሸጣል፡፡ አርብና እሮብ መኮሮኒ እና ፓስታ በብዛት ይገኛል፡፡ አራት ኪሎ ከምን..ክ ት/ቤት ደጅ በተጨማሪ ትንሽ ዝቅ ብሎ በሚገኘው አዲሱ የእግረኛ ተንጠልጣይ ድልድይ ስር ቡሌው ላልታደሉ ዜጎች ይቸበቸባል፡፡ ድልድዩ ላይ አንድ ጥግ ይዘው ሁለት ወጣቶች ቡሌ ገዝተው ሲመገቡ በፎቶ ለማስቀረት ችያለሁ፡፡
ወላይታው ሊስትሮ እንዳብራራልኝ ከሆነ ነዳያንና የጎዳና ተዳዳሪዎች ብቻ ሳይሆኑ እርሱም ሆነ ሌሎች የስራ ባልደረቦቹ ቡሌ ገዝተው ይበላሉ፡፡ ሊስትሮዎቹ የዩኒቨርስቲውን ቡሌ አልፎ አልፎ ቢመገቡም የነርሱ ምርጫ ግን የ..ሸራተን ቡሌ.. እንደሆነ አጫውተውኛል፡፡

## የሸራተን ቡሌ

ይህ በሸራተን ስም የሚሸጠው ቡሌ ከዚሁ ሆቴል የሚወጣ ይሁን አይሁን ማረጋገጥ አልቻልኩም፡፡ ሆኖም አንድ የሸራተን ሆቴል ሰራተኛ ነኝ በሚል ግለሰብ ትራፊ ምግቡ ለሸያጭ እንደሚቀርብ ተመልክቻለሁ፡፡ ግለሰቡ ፌስታል ከራሱ የሚያቀርብ ሲሆን ምግቡን በስስ ፌስታል እየቋጠረ አስቀድመው ለተመዘገቡ ደንበኞቹ ሰዓቱን ጠብቆ ልክ ከምሽቱ 12፡30 ሲሆን ማደል ይጀምራል፡፡ አንድ ፌስታል የሸራተን ቡሌ በ3 ብር ይሸጣል፡፡ ከዩኒቨርስቲው ቡሌ ጋር ሲነፃፀር የአንድ ብር ጭማሪ አለው፡፡ ወላይታው ሊስትሮ እንደሚለው የ..ሸራተኑ ቡሌ.. ለማንኛውም እንግዳ ሰው አይሸጥም፡፡ ሰውየው ፖሊስ እንዳይዘው ይፈራል፡፡ ..በወር 60 ብር ማዋጣት ስላለብኝ በቀን 2 ብር መቆጠብ አለብኝ፤ ለአራት ሆነን ነው ቤት ተከራይተን የምንኖረው፤ በቀን 25 ብር ነው የምናተርፈው፤ ሁለት ብር በቀን ካልቆጠብኩ የት አድራለሁ፡፡ ሻይ ቤት ብበላ ቀኑን ሙሉ ሰርቼ ያገኘኋት 25 ብር ታልቅብኛለች፡፡ ስለዚህ በሳምንት ብዙ ቀን እኔም ሆንኩ ሌሎች የሀድያ፣ የወላይታ ልጆች የምንበላው የሸራተን ቡሌ ነው፡፡.. ብሎኛል ወላይታው ሊስትሮ፡፡

## እውነት ነው ተረት?

አንባቢ ሆይ.. ..ከዚህ በላይ ያነበብኩት ..እውነት ነው ተረት?.. ብለህ እንደምትጠይቅ እገምታለሁ፡፡ ይህን አስቀድሜ በመጠርጠሬ ያየሁትን በካሜራዬ ለማስቀረት ሞክሪያለሁ፡፡ ይህ ካላሳመነህ ዘወትር ከሰኞ- እሁድ የምጠቁምህ ቦታ ሄደህ ማረጋገጥ ትችላለህ፡፡ ምናለሽ ተራ ወደ ፎዴ ተራ በሚያስገባው ቀጭን መንገድ 50 ሜትር ገባ ብሎ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት ትራፊ ምግብ በጆንያ ውስጥ ተሞልቶ በስስ ፌስታል እየተቆነጠረ ይሸጣል፡፡ መርካቶ አዲስ አበባ ገበያ ማዕከል ወደ ጣና ገበያ በሚያዋስነው አቅጣጫ ባሉ በረንዳዎች እራት ብቻ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ በፌስታል ይቸረቸራል፡፡ የዚህ አካባቢ ቡሌ ሻጮች ..ፖሊስ አላሰራ አለን.. ሲሉ ምሬታቸውን ነግረውኛል፡፡
አንዋር መስጊድ አረብ ተራ ወደ ሲኒማ ራስ በሚወስደው አቅጣጫ በቀን ከ300 መቶ ያላነሱ ሰዎች ለ..ኡፋ.. ወይም ..ቡሌ.. ሰልፍ ይሰለፋሉ፡፡ ከሲኒማ ራስ ጎን ባለች አደባባይ ከዚህ ቁጥር የማይተናነስ የኡፋ ግብይት ይካሄዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተክለሃይማኖት፣ አሜሪካን ግቢ፣ ሀብተጊዮርጊስ ድልድይ፣ አውቶቡስ ተራ መናኸሪያው ዙሪያ እና ሰባተኛ የቡሌ/ኡፋ ግብይት ይካሄዳል፡፡
በመርካቶ ሁሉም ነገር ይሸጣል፡፡ አንድ እግር ካልሲም ይሸጣል፡፡ በየሆቴሉ በቆሻሻ ገንዳ የተደፉ ትራፊ ምግቦችም ይሸጣሉ፡፡ ትራፊ ምግቦች በጉርሻ መልክ መሸጥ የጀመሩት ዛሬ አይደለም፡፡ አመታትን አስቆጥረዋል፡፡ የአገሪቱ ብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ እንኳ ሳይቀር ይህን አስገራሚ የጉርሻ ትዕይንት ቀርፆ ለታሪክ አስቀርቶታል፡፡ ያኔ ገጽታ ግንባታ የሚለው የፖለቲካ ካርታ ሳይመዘዝ፡፡ ረጲ አካባቢ በሚገኝ አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህፃናት እየተራቡ ይወድቁ እንደነበርና ይህንንም በአንድ ወቅት ኢቲቪ 2 በመዘገቡ ማስጠንቀቂያ እና ተግሳጽ እንደደረሰው ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ዶ/ር መራራ የሚያወሱት የከተማ ረሀብ ምኑ ላይ ነው አስደናቂነቱ?
በምታልፍበት በምታገድምበት ጎዳና ሁሉ ጥግ ጥጉን ብትመለከት ቆሻሻ ብቻ አይደለም የምታየው፤ የቆሻሻን ያህል ክብር ያላገኙ ዜጎችንም ወድቀው ልታይ ትችላለህ፡፡ በመጠጥ የሰከሩ ዜጎች ብቻ አይደሉም ትቦ ውስጥ ወድቀው የሚታዩት፤ እመነኝ፣ በረሃብና ጠኔ የሰከሩም አሉበት፡፡

## እና ምን ይጠበስ?

ቡሌ ወይም ኡፋ በይፋ በወረፋ ይሸጣል፡፡ እና ምን ይጠበስ? በረሀብ ሰው በሚሞትበት አገር . . ኡፋ. .

በይፋ መሸጡ ምንም አስገራሚ ነገር የለውም፡፡ ሆኖም በአንድ ምናለሽ ተራ ለዘመናት ሲሸጥ የነበረ ..ኡፋ.. ዛሬ በየአደባባዩ፣ በየስርቻው በፍጥነት መስፋፋቱ ብዙ የሚነግረን ቁም ነገር ያለ ይመስለኛል፡፡ ለአገሬ ገጽታ ከማንም ዜጋ እኩል እቆረቆራለሁ፤ ገጽታ እንዳይበላሽ ተፈርቶ ግን አውነትን መደበቅ የሚገባኝ ፍልስፍና አይደለም፡፡

ዛሬ በየትኛውም አካባቢ አይናችንን ከገለጥን ርቧቸው መንገድ ዳር የወደቁ፣ ታመው መንገድ ዳር የሚያቃስቱ ዜጐችን አለማየት የማንችልበት ደረጃ ደርሰናል፡፡ ይህንን ጽሑፍ ያነበበ ዜጋ በአካባቢው ጥቂት የእግር ጉዞ ቢያደርግ ከአንድ ስርቻ ውስጥ አንድ የተራበ፣ አንድ የታመመ ሰው ወድቆ እንደሚያይ እወራረዳለሁ፡፡

መንግስት አንዳንድ ጊዜ ለህሊናው ሲል እውነትን መቀበል አለበት እላለሁ፡፡ ፕሮፓጋንዳ ጥሩ ነው፡፡ ሆኖም በየእለቱ በየደጃችን የምናየው ነገር ..ውሸት ነው፣ አይናችሁ ተጭበርብሮ ነው፣ መርዶ ነጋሪ ስለሆናችሁ ነው.. እንዲለን አንፈልግም፡፡ ድህ ኒወርክም ለንደንም አለ፡፡ ጉርሻ የሚሸጥበት አገር ግን ከኢትዮጵያ ሌላ በምድራችን ከወዴት ይገኛል? መንግስት የሚችለውን ሁሉ ያድርግ፡፡

ቢራ እየጠጡ መታገልን የመረጡ ተቃዋሚዎችም ከተጠያቂነት የሚያመልጡበት ጊዜ እየረፈደ ነው፡፡ ዶ/ር መረራ ..የሚበላውን ያጣ ህዝብ..... እያሉ ሲተርቱ ይኸው ስንት አመታቸው፡፡ ለጊዜው የሚበላውን ያጣ ህዝብ ተስለምልሞ ሲሞት እንጂ መሪዎቹን ሲተናኮል አላየንም፡፡ በመሆኑም የዶክተሩ ትንቢት መቼ እንደሚደርስ አይታወቅም፡፡ ትንቢቱ ከደረሰ ግን አንድ ነገር እርግጠኛ መሆን ይኖርብናል፡፡ የሚበላውን ያጣ ህዝብ የሚመራውን ብቻ ሳይሆን ቢራ እየጠጣ የሚታገልለትንም የሚምር አይመስለኝም፡፡ ዋ.. እንዲል__